# ተቃዋሚ ትግራውያን — ቢከፍቱት ተልባ?

ቢሻው ስንታየሁ

ክሱ ከመደርደሩ በፊት እኔ "ወያኔና የትግራይ ሕዝብ አንድ ናቸው" ወይም "ሁሉም የትግራይ ተወላጅ በልቡ ወያኔ ነው" ብለው አቅዋም ከያዙት መሀል የምገኝ አለመሆኔን ነው። ግን የማይካደው ሀቅ አለ - የትግራይ ተወላጆች በተይም ምሁራኖች ራሳቸውን የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ኣድርገው በመቁጠር፣ የነመለስን ዘረኝነት እየተጋሩ መሆናቸው ነው። ወያኔን ሲቃወሙ ማየት አቅቶናል ብንል ትክክል ነው።

አቶ ስዬ ኣብርሃ ሰሞኑን ለጀርመን ድምጽ ራዲዮ በስጠው ቃለ መጠይቅ፣ ወያኔ ለተራቡ የትግራይ ተወላጆች የተሰጠውን ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ለመሳሪያ ግዢ አውሎታል የሚለውን አስተባብሏል። የወያኔ መስራች መሪ የነበረው አቶ አረጋዊ በርሔ በበኩሉ ቆይቶ ቢሆንም የመለስ ቡድን የእርዳታውን 95 በመቶ ለራሱ ድርጅት ወጪ ማዋሉን ደጋግሞ ኣጋልጧል። ቀደም ሲል ኣቶ ገብረ መድህንም ይህንኑ አጋልጠው ነበር። በምዕራባውያን የስለላ ድርጅቶች ተቀነባብሮ፣ በርሀቡ ሽፋን ለወያኔ የተሰጠውን ድጋፍና ገንዘብን አስተላላፊ ቧንቧ የሆኑት የምዕራብ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ደግሞ ይህ ህገ ወጥ ሚናቸው እንዳይጋለጥ መከላከል ይዘዋል። ሰር ቦብ ጌልዶፍ የተባለው የተንጫጫው፣ ሌሎችም ግብረ ሰናዮች ያስተባበሉት፤ በእንግሊዝ መንግስት ቁጥጥር ስር ያለውም ቢቢሲ ስለ እርዳታው በወያኔ መሰረቁን ማስተላለፉን ስህተት ነው ለማለት የተገደደው፣ ምዕራቡ ዓለም በዜጎቻችን ህይወት ላይ ከወያኔ ተባብሮ ምንኛ እንደተጫወተ ወይም ግፍ እንደሰራ እንዳይታወቅ ነው። ወያኔም የተነገረው ሀሰት ነውና ይቅርታ ልጠየቅ ማለትን ደፍሯል። በ 1997 ኡ ምርጫ ወያኔ ሽንፈትን ሲከናነብ፣ ከዚያ በፊት ጸረ ወያኔ ሆነናል ይሉ የነበሩና ትግሬነታቸው ካሸነፋቸው አንዱ የሆነው ብስራት አማረ የተባለው ለምሳሌ፣ ወያኔ የርሀቡን እርዳታ ለራሱ ጥቅም አላዋለም ሲል የወያኔ ጠበቃ ሆኗል። ቁርጥ ቀን ሲመጣ ትግራውያን ተቃዋሚ በሉን ባዮች፣ በኣብዛኛው ንጹህ ኢትዮጵያዊ አቅዋም መያዝ ሲያቅታችው ታዝበናል።

ፕሮፌሰር ተኮላ ሐጎስ በሰሞኑ የትግራይ ምሁራን የሕዝብን ትግል እንዲደባለቁ ያሰሙት ጥሪ ተገቢ ምሆኑ ይታምንበታል። ዶክተር ስታንተን የተባሉ አሜሪካዊም የነመለስ መዘዝ በትግራይ ሕዝብ ላይ መዓት እንዳያመጣ ያሰጋል ብለዋል። ሆዳም፣ ፈሪ፣ ትምክህተኛና ወዘተ እየተባለ የሚወገረው አማራና ሌሎችም በወያኔ መናቃቸው ደግሞ የሚደበቅ አይደለም። የመረረ ጸረ-ወያኔ ግን ጸረ-ትግሬ እየሆነ በማደግ ላይ ያለ ስሜትም መኖሩን በጊዜ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ለነገሩ ወያኔ ለስልጣን ሲበቃ ፕሮፈሰር ተኮላ ስልጣን የተጋሩና በስፋትም ሊጋሩ ተዘጋጅተው የነበሩ ናቸው። ፕሮፌሰር ገላውዲዮስ ኣራያም ለምሳሌ የወያኔ መጽሔት "ዘ ኮመንቴተር" ሃላፊ ሆነው እነ ኢሕአፓና ትምክህተኛ አማራ የተባለን ሁሉ ቀጥቃጭ ነበሩ። በ አጼ ምኒሊክና ቴዎድሮስ ላይም የወረደውን ውርጅብኝ አንረሳውም። ዶክተር ተኮላ ዛሬ ዕጹብ ድንቅ ብለው የሚያደንቁት ጋሀዲ የተባለው በወያኔ ኣንዱ መስራች የተጻፈው መጽሐፍ ለምሳሌ ከወያኔያዊ ውሸትና ትምክህት ያልተላቀቀ ነው። ቁጥሩ ቢያንስም ጀግናው የትግራይ ጦር ስንትና ስንት ሺ ኢዲህና ኢሕአፓን እንዳሸበረም /የግጭቶቹን ምክንያት ደብቆ/ ተረት ተረት ይነግረናል። ወያኔ ስለፈጸመው የሕዝብ ፍጅት ምንም ሳይል ሌሎችን በውሸት ይከሳል። (መጽሃፉ ራሱን የቻለና ሚዛናዊ ትችት ያስፈልገዋል)።

ፕሮፈስር ተኮላም ሆኑ እነ ገብሩ አስራት ከመለስ ዜናዊ መጣላታቸው እውነት ሊባል ቢችልም ከወያኔነት ወይም የትግሬ የበላይነት ጋር ግን ለአንዴም ለሁሌም ተለያተዋል ሊባል ኣይቻልም። ለዚህም ነው ኣቶ ገብረመድህን በሚያውቀው ደረጃ ሁሉና ኣቶ አረጋዊ ደግሞ በተወሰነ ደረጃ ወያኔን ሲያጋልጡና በሕዝብ — በተለይም በትግራይ ሕዝብ-- ላይ ወያኔ የፈጸመውን ግፍ ሲያጋልጡ — እነ ስዬና ገብሩ ወዘተ ተከላካይ ሆነው የሚከራከሩትና ሀቁን የሚደብቁት። ለዚህም ነው ትግራዊ ተቃዋሚዎች ቢከፍቱት ተልባ ሆኑ እንዴ? ብለን መጠየቅ የተገደድነው።

መለስን ብቻ ሳይሆን ወያኔን እንደድርጅትና ዘረኝነትንም እንደ አቅዋም መቃወም ያስፈልጋል። ይህ ግዳጅ በተለይ በትግራይ ምሁራንና ሕዝብ ላይ የሚውድቀውም በስልጣን ያለው ቡድን በትግራይ ሕዝብ ስም ስለሚገዛና ሀገርንም ስለሚጎዳ ነው።

ተወደደም ተጠላም ሀላፊነት አለ። ወያኔ አይውክለንም ብሎ በተቃዋሚ ጎን መስለፍ መቆም የግድ ይሆናል። የትግራይ ተወላጆችን በጅምላ የሚኮንን አቋም ከሚያራምዱ አንዳንድ ወገኖች በተቃራኒ <u>የትግራይ ብዙሃንና ጥቂት ወያኔዎችን ለይተን ማየት አለብን</u> ብለው የሚሟገቱ ኢትዮጵያዊያን ሃይላትም እኮ በውን የሚታዩ ምሳሌዎችን በብዛት መደርደር ይሻሉ። ተነሱ ጻረ ወያኔ ነን በሉና በተግባር አሳይታችሁ ተቆጠሩ የሚል ነው መልዕክቱ። በየፓልቶኩና ድረ ገጹ አፍቅሮ ወያኔን ማስተጋባትና ትምክህትን መደገፍ ለትግራይ ሕዝብ የነ ዕጣ የሚበጅ አይሆንም። በእርግጥ ነው ኢትዮጵያዊነት በጊዜ ሰጠሾች ጥቂት ዘረኞች እና በታሪካዊዎቹ ባዕዳን ጠላቶቹ ምክር እንዲህ በቀላሉ የማይፈራርስ፣ የማይጠፋ ከጽኑም ጽኑ ነው። ተበታተነ ሲሉት የሚያሰባስብ፣ ወደቀ ሲሉት የሚያስቆም፣ ረጅም ታሪኩ የፈጠረው የራሱ አፈጣጠር አለው። በገዢዎቻችን ዘረኛ ፖሊሲ ሰበብ፣ ካመት ዓመት በተቆጠረ ቁጥር ግን እየተፈጠረ ያለው በደልና ቁርሾ፣ ሁዋላ መዘዙ ቀላል አይሆንም። የወያኔን ውድቀት ተከትሎ ሁኔታዎች እስከሚሰክኑ ሊያስከትል የሚችለው ጥፋት ሊያሳስበን ይገባል። ወደድንም ጠላንም ባስተሳሰረን እና አስተሳሰሮንም በጋራ በሚያኖረን ኢትዮጵያዊነታችን ላይ እያደረሰ ያለው ጥፋትም እንደዚሁ። አዎ! ተነሱና ጻረ-መለስ ብቻ ሳይሆን ጻረ-ወያኔ ነን በሉን። ቤተኛም የነበራችሁ ይህ ጻረ-ኢትዮጵያ ሃይል በባዕዳን እየተረዳ ምን እንዳደረጋችሁብን፣ ለአሁንም ምን እንደቶደለተብን እና እያደረገብንም እንዳለ በእውነት ስለ እውነት እንነጋገርና በህብረት እንቁም። በሁለት ባላ መቆሙን ትተን በአንድ ኢትዮጵያዊ ባላ ላይ እንቁም።